# ሌላው ኩራታችን...

ግርማ ወ/ማሪያም አቤ

ሽቅብ ወደ ላይ በመንጠራራት የሰማዩን አድማስ እየሰነጠቀ ጉምና ጭጋጉ ሳያግደው የሚከንፈው የአገር ኩራት የሆነው አውሮፕላን አሁንም ጉዞውን ቀጥሏል።

የወገን አለኝታ፣የአገር አድባር የሆነው አየር መንገዳችን የሁሉን ቀልብ ገዝቶ በአገር ውስጥና በውጭ እንደልቡ የሚንፈላሰሰው ምቹ በሆነው የአየር ማረፊያና መብረሪያ ሥፍራ መሆኑ አሌ አይባልም።

አውሮፕላኑ ገና ከመነሻው ሽቅብ ወደ ላይ ለመንጠራራት ሲያኮበኩብና ለማረፍና መሬት ለመንካት ዝቅ ሲል ስንቶቻችን ይሆን የማኮብኮቢያውንና የማረፊያውን ሥፍራ አስተውለን የምናውቀው?

ስንቶቻችንስ ይሆን ውብና ማራኪ ዓለም አቀፋዊ ዝናን ያተረፉ እንግዳ ማረፊያ ወይም ተርሚናሎችን ልብ ብለን በአንክሮ የታዘብን? አዎ! ምን ያህሎቻችንስ ይሆን የኤርፖርቶች ድርጅትንና የአየር መንገዳችን፣ የአቪየሽንን ልዩነት የምንገነዘብ? ለማንኛውም ስለ ኤርፖርቶች ድርጅት የምንለው አለና ብዕራችን አነሳን።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ለረዥም አመታት የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ቁጥጥርንና የኤርፖርት አገልግሎት ሁለቱንም አጣምሮ ሲሰራ የነበረው የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ነበር።

ወራት እየነጎዱ፣ ቀናት እየከነፉ ሲሄዱ መንግሥት የኤርፖርት አገልግሎቱን በተመለከተ ልዩ ትኩረት በመስጠቱ የኤርፖርቶች ድርጅት በወርሃ ጥር 1995 ራሱን ቻለና የራሴ የሚለውን ታሪክ ማስመዘገብ መጀመሩን የድርጅቱ ዋና ሥራ አሥኪያጅ አቶ ሺፈራው ዓለሙ አጫውተውናል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ ከሆነ ውብና ማራኪ የሆኑ እንግዳ ማረፊያ ወይም ተርሚናሎችን፣ አውሮፕላኑን ያለምንም ችግር በምቾት የሚያርፍበት ሜዳን በማስዋብና በመገንባት ወደ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገሩ ሌላውም የአገር ኩራት መሆኑን ደጋግመው ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ምንም እንኳን ከአየር መንገድና ከአቪየሽን የተያያዘና የተቆራኘ ሥራ ቢከናወንም በዋናነት የአውሮፕላን የመንደርደሪያና ማረፊያ ሜዳ፣ የመንገደኞች ማስተናገጃ ሕንጻና የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ ማማ ግንባታና ሌሎች ሥራዎች እንደሚያከናውን አቶ ሺፈራው ያስረዳሉ።

ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት በመላው አገሪቱ ከሚያስተዳድራቸው 17 ኤርፖርቶች መካከል 15ቱ ጀት አውሮፕላኖች የሚያሳርፉ መሆናቸው ሌላው የአገር ኩራት መሆኑን የሚያመለክት ነው።

በተለይ የጎንደር፣ የላሊበላ፣ የአክሱም፣ የአርባና ምንጭና የመቀሌ ኤርፖርቶች አዳዲስ የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳዎችና የተርሚናል ሕንጻዎች ተገንብተው ቀደም ሲል ከነበረው በተሻለ ሁኔታ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸው መንግስት ለክልሎች የሰጠውን ትኩረት የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ በቱሪስት የሚገኘውን ገቢ ከማሳደግም አንጻር የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ማለት ነውና ተጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል እንላለን።

በበርካታ እንግዶች ዘንድ አግራሞትን የሚያጭረው የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያም የአውሮፕላን የመንደርደሪያና ማረፊያ ሜዳ፣ አዲስ የመንገደኞች ማስተናገጃ ሕንጻና የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ ማማ ግንባታና ሌሎች ሥራዎች ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ በ1ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ወጪ መሰራቱ የአገሪቱን መልካም ገጽታ ከማስተዋወቅ አንጻር ከፍተኛ አስተጽኦ ማበርከቱን አቶ ሺፈራው ያስረዳሉ።

አንዳንድ የውጭ አገር ዜጎችም የኢትዮጵያን ምድር ገና ሲረግጡ የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያም ሲያዩ ኢትዮጵያ በምዕራባውያን ሚዲያ የነበራትን ጥሩ ያልሆነ ገጽታ ሙሉ ለሙሉ እንዲቀይሩ ምክንያት እንደሆናቸው ይናገራሉ። ለዚህም ነው የሳዑዲው ባለሃብት ሚስተር ሶሻሚ በቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ በጣም ከመደነቃቸው የተነሳ በቃላት ሃሳባቸውን ለመግለጽ የተቸገሩት።

ወደ አውስትራሊያና ወደ ዱባይ የሚጓዙት ወጣት ዮሴፍ ሞላና የምስራች ማሞ በሰጡን አስተያየት የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ከሌሎች አገሮች አውሮፕላን ማረፊያዎች እንደማይተናነስና በጣም እንደሚኮሩበት ደጋግመው በፈገግታ ጭምር መግለጻቸው ድርጅቱ ከፍተኛ እመርታ እያሳየ እንደሆነ የሚያመላክት ነው። ከድርጅቱ ሥራዎች መካከል የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ የአንበሳውን ድርሻ እንደሚይዝ ብዙ ሰዎች ይስማማሉ።

በየክልሉ ያሉ የአውሮፕላን የመንደርደሪያና ማረፊያ ሜዳዎች ዘመናዊ ከመሆናቸው ባሻገር ለአገር ውስጥና ለውጭ ቱሪስቶች ከፍተኛ ጥቅም እየሰጡ መገኘታቸው ሌላው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በመሆኑ ድርጅቱ በሚያደረገው እንቅስቃሴ ሊበረታታና ሊመሰገን ይገበዋል።

ድርጅቱ ጥረቱን አጠናክሮ በመቀጠል ቀደም ሲል ስድስት የነበሩትን የጀት አውሮፕላን ብቻ ማሳረፊያ ሜዳዎች ወደ 15 ከፍ በማድረግ አጋርነቱን አስመስክሯል።

በመቀሌ፣ በጎንደር፣ በአክሱም፣ በባህር ዳር፣ በላሊበላ ያገኘናቸው የአካባቢው ሽማግሌዎችና የድርጅቱን ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች እንዳወጉን ደግሞ ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ለአውሮፕላኖች፣ ለመንገደኞችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አስተማማኝና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ እያከናወነ ያለው ተግባር በተለይም ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ የሚደነቅ መሆኑን መስማማታቸው የድርጅቱን ለውጥ የበለጠ የሚያጎላው ሆኖ አግኝተነዋል።

ስለ ኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ትናንት ምን ነበር? ዛሬስ ምን ደረጃ ላይ ይገኝ ይሆን? በሚል የአገራችን ፕሬዘዳንት ቢሮም ማንኳኳታችን አልቀረም። ምክንያቱም ፕሬዚዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ አብዛኛው ሕይወታቸውን በኢትዮጵያ ሲቪል

አቪዬሽን ባለሥልጣን ስላሳለፉ። ፕሬዚዳንት ግርማ እንደሚሉት ከዕለት ወደ ዕለት የኤርፖርቶች ደርጅት እያሳየ ያለው ለውጥ መልካም እንዲሆንና ወደፊትም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ነው።

በለውጥ ሂደት ላይ ያለው ድርጅቱ ለአገር ዕድገት ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንጻር እያሳየ ያለው እንቅስቃሴ እሰየው የሚያሰኝ ነው። ከሁሉም በላይ አውሮፕላኖችና መንገደኞች ያለምንም እንከን ምቾታቸው ተጠብቆ ካሰቡት እንዲደርስ ለማስቻል ዘመናዊ የማረፊያ ሜዳዎችንና የእንግዶች ማረፊያ በዘመናዊ መልኩ እያሰራ ያለውን መልካም ጅምር አጠናክሮ እንደሚቀጥል የድርጅቱ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ወንድም ተክሉ መናገራቸው የድርጅቱን የወደፊት እቅድ ብሩሕ መሆኑን የሚያመላክት ነው።

በአጭሩ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ደርጅት አሁን እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ ሌላው የአገርና የወገን ኩራት እየሆነ በመምጣቱ ባሳየው ተጨባጭ ለውጥ ሁሉንም ደስ ያሰኛል። እናም ሽቅብ ወደ ላይ በመንጠራራት የሰማዩን አድማስ እየሰነጠቀ ጉምና ጭጋጉ ሳያግደው የሚከንፈው አውሮፕላንም በአስተማማኝ ሁኔታ ጉዞውን እንዲቀጥል ለማስቻል የኤርፖርቶች ድርጅት ምቹ የአውሮፕላን የመንደርደሪያና ማረፊያ ሜዳ፣ የመንገደኞች ማስተናገጃ ሕንጻና የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ ማማ ግንባታና ሌሎች ሥራዎች አጠናክሮ በመቀጠል ሌላው ኩራታችን መሆኑን ደጋግሞ ያስመስክር እንላለን። ሰላም።